

የስህተቶች ቁልፍ ...

ስህተትን ማረም ጥበብ ነው። እያንዳንዱ በር ቁልፍ አለው። ሁሉም ልቦች ወደዚያ ያመራሉ። ነብዩ /ሰ.ዐ.ወ/ ከበኑ መስጠሊቅ ዘመቻ በመመለስ ላይ ሳሉ ከባልደረቦቻቸው ጋር አንድ ቦታ ላይ አረፉ። በዚህ ወቅት ሙሃጂሮች ጀህጃህ ቢን መስኡድ የሚባል ልጅ ውሃ እንዲቀዳ ላኩት። አንሷሮችም ሲናን ቢን ወበር አልጁሃኒ የሚባልን ልጅ ላኩ። ሁለቱ ልጆች በውሃ የተነሳ ተጣሉና መደባደብ ጀመሩ። አንዱ አንደኛውን ጀርባው ላይ መታው። አልጁሃኒ "አንሷሮች ድረሱልኝ" በማለት ተጣራ። ጀህጃህም "ሙሃጂሮች ድረሱልኝ" አለ። አንሷሮችም ሙሃጂሮችም እየሮጡ ሄዱና እርስ በርስ ይጣሉ ጀመር። ከውጊያ እየተመለሱ በመሆናቸው የጦር መሳሪያ ታጥቀዋል። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ደርሰው ጥሉን አበረዱ። ሆኖም አንድ ችግር ተፈጠረ። የሙናፊቆች መሪ የሆነው አብዱላህ ኢብኑ ሰሉል ነገሩን አካረረው። የተወሰኑ አንሷሮችም የሱን ሃሳብ ተጋሩ።

"በኛ ላይ ይህንን ነገር አደረጉ? በራሳችን አገር በቁጥር በለጡንና በኛ ላይ ተነሱብን? ውሻህን ካደለብከው ይነክስሃል። ካስራብከው ያባርርሃል ይባል የለ!" አለ። ይህ ከፋ ሰው አከሎም "ወላሂ መዲና ስንደርስ የተከበረው ወራዳውን ከመዲና ያባርረዋል" አለ። ከዚያም አጠገቡ ላሉ ሰዎች "ይህን ሁሉ ጣጣ በራሳችሁ ላይ ያመጣችሁት እናንተው ናችሁ። ከመሬታችሁ አሰፈራችኋቸው። ንብረታችሁን አካፈላችኋቸው። በአላህ እምላለሁ የሰጣችኋቸውን ነገር ብትከለክሏቸው ኖሮ ወደ ሌላ አገር ይሄዱ ነበር" እያለ ወቀሳውንና ዘቻውን ቀጠለ። አጠገቡ ያሉ ሙናፊቆችም ስምምነታቸውን ይገልፁለትና ያበረታቱት ጀመር። ይህንን ያደምጥ የነበረ ዘይድ ቢን አርቀም የሚባል ትንሽ ልጅ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ ሄደና ዜናውን ነገራቸው።

ኡመር ኢብኑል ኸጧብ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጎን ተቀምጠው ነበር። በጣም ተቆጡና "ይህ ሙናፊቅ እንዴት ነው ስለ አላህ መልዕክተኛ በንቀት የሚናገረው?" አሉ። ኡመር የእፍኝትን ጅራት ከመቁረጥ መግደል እንደሚሻል አሰቡ። ኢብኑ ሰሉልን መግደል ብጥብጡን ባጭሩ ይቀጨዋል የሚል ስሜት አደረባቸው። ሆኖም በሙሃጂሮች ከሚገደል በራሱ በአንሷር ሰዎች ቢሆን የተሻለ እንደሚሆን አሰቡ። እናም ኡመር "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ኡባድ ኢብኑ በሽር አል አንሷሪ እንዲገድለው እዘዙት" አሉ። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አርቆ አሳቢ ናቸው። የሚመለሱት

ከውጊያ ነው። ሰዎች ከነትጥቃቸው ናቸው። በዚያ ላይ ስሜት ውስጥ ገብተዋል። የበለጠ ቀውስ መፍጠር ተገቢ አይደለም። "ኡመር ሆይ! አይሆንም። ሙሐመድ ባልደረቦቹን ይገድላል የሚል ወሬ እንዳይሰራጭ እሰጋለሁ። ይልቅ ለጉዞ እንንቀሳቀስ" አሉ። ጥላ ቦታ ላይ አርፈው ነበር። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዴት በከባድ ሙቀት ተነሱ ሊሏቸው ቻሉ? በዚህ መሰሉ ከባድ ሀሩር ወቅት ተነሱ ብለው አያውቁም። ሆኖም ተነሱ።

አብዱላህ ኢብኑ ሰሉል የተናገረውን ነገር ዘይድ ቢን አርቀም ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንደነገራቸው ሰማ። በመሆኑም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ በመምጣት ትንሹ ልጅ እንደዋሻቸውና እሱ አንድም ቃል እንዳልተናገረ በአላህ እየማለ ያስረዳቸው ጀመር። ኢብኑ ሰሉል በህዝቦቹ ዘንድ ትልቅ አክብሮት የሚሰጠው መሪ ነው። አንድ የአንሷር ሰው ተነሳና "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ትንሹ ልጅ ተሳስቶ ሰውዬው በትክክል የተናገረውን ማስታወስ አቅቶት ይሆናል" አለ። ሌሎቹም ለኢብኑ ሰሉል መከራከር ጀመሩ። ሆኖም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለማናቸውም ትኩረት ሳይሰጡ መንገዳቸውን ቀጠሉ። ከዚያም ከአንሷር መሪዎች አንዱ የሆነው ኡሰይድ ቢን ሁደይር መጥቶ ሰላምታ ከሰጣቸው በኋላ "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ለምን ለጉዞ ምቹ ባልሆነው በዚህ ሰዓት እንድንንቀሳቀስ ፈለጉ? ከዚህ በፊት ይህን አድርገው አያውቁም" አላቸው።

ነብዩም "ጓደኛህ የተናገረውን ነገር አልሰማህም እንዴ?" አሉት። "የትኛው ጓደኛዬ? የአላህ መልዕክተኛ" አላቸው።

"አብዱላህ ኢብኑ ኡበይ" "ምን አለ?" አላቸው።

"ወደ መዲና ስንመለስ የተከበረው ወራዳውን ያባርረዋል" ሲል ዝቷል አሉት። ኡሰይድ በጣም ተናደደና "የአላህ መልዕክተኛ ከፈለጉ እሱን ከመዲና ሊያባርሩት ይችላሉ። በአላህ እምላለሁ ወራዳው እሱ ሲሆን የተከበሩት እርስዎ ነዎት" አለ። ከዚያም ኡሰይድ የነብዩን ንዴት ለማቀዝቀዝ ፈለገና "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ይቅርታ ያድርጉለት። አላህ እርስዎን ወደኛ ሲያመጣዎት ህዝቦቹ ዘውድ ሊጭኑለት እንቁዎችን እያስጌጡ ነበር። እናም እሱ እርስዎ ንግስናውን እንደቀሙት ነው የሚያስበው" አላቸው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዝም ብለው መንገዳቸውን ቀጠሉ። አንዳንድ ሰዎች ኢቃዎቻቸውን እየሰበሰቡና ሌሎቹ ደግሞ ግመሎቻቸው ላይ እየወጡ ነበር። የመላው ጦር መወያያ ርዕስ እስኪሆን ድረስ ወሬው ተሰራጨ።

"ለምን በዚህ ሰዓት ተነሳን? ምን ተባለ? እኛ ምን ማድረግ አለብን። ኢብኑ ሰሉል የተናገረው ልክ ነው። አይ ተሳስቷል" የሚሉት ወሬዎች በህዝቡ ዘንድ በከፍተኛ ሁኔታ ተሰራጩ። ጦሩ ግራ እንደተጋባ መንገዱን ቀጠለ። ከዚህም በተጨማሪ ጥቂት ጥለኛ ጎሳዎች ይጠብቋቸዋል። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጦሩ ሊከፋፈል

እንደሚችል አሰቡ። እናም በሆነ ነገር አዕምሯቸውን ቢዚ ማድረግና ሃሳባቸውን ማስቀየር ፈለጉ። በዚሁ ከቀጠሉ ግን በአንሷሮችና በሙሃጂሮች መካከል ችግር ሊፈጠር ይችላል። ሰዎቹ ቆም ብለው በጉዳዩ ላይ የሚወያዩበትን ወቅት ይጠባበቃሉ። ሆኖም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጦሩን ይዘው ቀኑን ሙሉ በፀሐይ ተጓዙ። ፀሐይዋ ገባችና ለሶላት ቆሙ። ከሰገዱ በኋላ እንደገና መንገዳቸውን ቀጠሉ። ሙሉ ሌሊቱን እየተጓዙ ጎህ ቀደደ። የሱብሂን ሰላት ከሰገዱ በኋላ አሁንም መንገዳቸውን እንዲቀጥሉ ታዘዙ። እስኪዳከሙና ፀሐዩ እስኪያቃጥላቸው ድረስ ጉዟቸውን ቀጠሉ። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሙሉ በሙሉ በመድከማቸው መናገር ሲያቅታቸው ሲመለከቱ እንዲያርፉ አዘዟቸው። አረፍ እንዳሉ ሁሉም እንቅልፍ ወሰዳቸው።

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይህን ያደረጉት የትኩረት አቅጣጫቸውን ለማስቀየር ሲሉ ነው። ትንሽ ከተኙ በኋላ ቀሰቀሷቸውና ጉዟቸውን ቀጥለው መዲና ደረሱ። ተበታትነው ወደየቤታቸው ገቡ። ከዚያም አላህ ሱረቱል ሙናፊቁን አወረደ። እነሱ እነዚያ "አላህ መልእክተኛ ዘንድ ላሉት ሰዎች እስከሚበታተኑ ድረስ አትቀልቡ" የሚሉ ናቸው። የሰማያትና የምድር ድልቦችም የአላህ ናቸው። ግን መናፍቃን አያውቁም። "ወደ መዲና ብንመለስ አሸናፊው ወራዳውን በእርግጥ ከሷ ያወጣል" ይላሉ። አሸናፊነትም ለአላህ፣ ለመልዕክተኛውና ለምእመናን ነው። ግን መናፍቃን አያውቁም። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይህን አንቀፅ ካነበቡ በኋላ የህፃኑን የዘይድ ቢን አርቀምን ጆሮ ያዙና "ይህ ነው በጆሮዎቹ የአላህን አደራ የሞላ" አሉ። ሰዎች ኢብኑ ሰሉልን መውቀስና መሳደብ ጀመሩ። እዚህ ላይ ለኡመር (ረ.ዐ) እንዲህ አሏቸው፡- "ኡመር ሆይ! አየህ ይገደል ባልከው ሰዓት ገድየው ቢሆን ኖሮ ብዙ ሰዎች ይቀየሙ ነበር። ዛሬ ግን እንዲገድሉት እንኳ ብጠይቃቸው ያለማመንታት ይገድሉታል" አሉ። አንዳንዴ አንድ ሰው በህዝብ ፊት ስህተት ሲሰራ ልታርመው ግድ ሊሆንብህ ይችላል። ነገር ግን በተገቢው ሁኔታ መሆን አለበት። እሱ በህዝብ ፊት ቢያደርገውም እንኳ።

አንዴ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከባልደረቦቻቸው ጋር ቁጭ ብለው ነበር። ህዝቡ በድርቅና በዝናብ እጦት እየተሰቃዩ ነው። አንድ ቤድዊን መጣና "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ህዝቡ እያለቀ ነው። ህፃናት ተርበዋል። ንብረት ወድሟል። አላህ ዝናብ እንዲሰጠን ለምኑልን። እርስዎ አላህን እንዲያማልዱልንና አላህም እርስዎን እንዲያማልደን እንፈልጋለን" አለ። ነብዩ /ሰ.ዐ.ወ/ "አላህም እርስዎን እንዲያማልደን እንፈልጋለን" የሚለውን ንግግር ሲሰሙ ፊታቸው ተቀያየረ። ምክንያቱም ምልጃ የሚያስገልገው ከትንሽ ወደ ትልቅ ነው። አላህ ፍጥረታቱን ያማልድ ማለት ተገቢ አይደለም። እሱ ያዛቸዋል እንጂ አይለምናቸውም። እሱ ከሁሉም በላይ የላቀ ነውና።

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) "ወዮልህ ምን እያልክ እንደሆነ ታውቃለህ?" አሉና "ሱብሃነላህ ሱብሃነላህ" በማለት አላህን ማወደስ ጀመሩ። ባልደረቦቻቸው የጉዳዩን

እንብቧቢነት እስኪረዱ ድረስ አላህን ማወደሳቸውን ቀጠሉ። ከዚያም "ወዮልህ! አላህ ፍጥረታቱን አያማልድም። አላህ ከዚያም በላይ የላቀ ነው። ለመሆኑ አላህን ታውቀዋለህ? ዙፋኑ ከሰማያት በላይ ነው።" በጣቶቻቸው የከብ ጉልላት ቅርፅ በመስራትም "ዙፋኑ ሲጢጥ የሚል ድምፅ ያሰማል። ኮርቻ በጋላቢው ጫና የተነሳ ድምፅ እንደሚያሰማው ሁሉ" አሉት። (አቡ ዳውድ)

አንድ ሰው ለብቻው ስህተት ሲሰራ እንዴት ነው ማረም ያለብን? አንዴ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አዒሻ (ረ.ዐ) ቤት መጡና ልብሳቸውን አወላልቀው ተኙ። አዒሻ እንቅልፍ ወስዷታል ብለው ካሰቡ በኋላ ቀስ ብለው ተነሱና ልብሳቸውን ለብሰው በሩን ቀስ አድርገው ከፍተው ወጡ። ይህን የተገነዘበችው አዒሻ ወደ ሌሎቹ ሚስቶቻቸው ሊሄዱ ነው የሚል ቅናት አደረባት። ተነሳችና ልብሷን ለብሳ ተከትላቸው ወጣች። እሳቸው ግን አላይዋትም። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በምሽቱ መንገዳቸውን ቀጠሉና አልበቂ የመቃብር ስፍራ ላይ ደረሱ። የባልደረቦቻቸውን የመቃብር ስፍራ ይመለከቱ ጀመር። በኢባዳ ኖረው በውጊያ ሞተው ከመሬት በታች የሆኑ ባልደረቦቻቸውን መቃብር።

መቃብሮቹን ትኩር ብለው እየተመለከቱ በትዝታ ወደ ኋላ ይመለሳሉ። እጆቻቸውን ወደ ላይ ከፍ በማድረግ ዱዓ አደረጉላቸው። አሁንም ከትንሽ ቆይታ በኋላ እንደገና አላህ ምህረቱን እንዲለግሳቸው ዱዓ አደረጉ። አዒሻ ከሩቅ ሆና ትመለከታቸዋለች።

ከዚያም ወደ ቤታቸው ለመመለስ ተነሱ። ይህን የተመለከተችው አዒሻ ነብዩ ሳይደርሱባት በፍጥነት ቤት ለመድረስ አሰበች። በፍጥነት መጓዝ ጀመሩ። አዒሻም ትፈጥናለች። ይበልጥ ፍጥነታቸውን ሲጨምሩ እሷም ይበልጥ ትፈጥናለች። ቀድማ ቤት ደረሰችና ልብሶቿን አወላልቃ አልጋዋ ላይ ተኛች። ሆኖም ትንፋሿ ጎልቶ ይሰማ ነበር። ነብዩ ወደ ቤት ሲገቡ የትንፋሿን ቁርጥ ቁርጥ ማለት አደመጡ። ስለሆነም "ምን ሆነሻል ኢዒሻ! ለምንድን ነው ትንፋሽሽ ቁርጥ ቁርጥ የሚለው" አሏት።

"ምንም" አለች።

"ንገሪኝ አለያ ብልሃተኛውና አዋቂው ያሳውቀኛል" አሏት። ቅናት እንዳደረባትና የት እንደሚሄዱ ለማወቅ እንደተከተለቻቸው ነገረቻቸው።

"ከፊት ለፊቴ የነበርሽው አንቺ ነሽ እንዴ?" አሏት። "አዎ" አለች።

ደረቷን ገፋ እያደረጉ "አላህና መልዕክተኛው ፍትህ ያጓድሉብኛል ብለሽ ታስቢያለሽ እንዴ?" አሏት።

“ሰዎች የቱንም ያህል ቢደብቁ አላህ ያውቀዋል” አለች።

“አዎ” አሏት።

እሳቸውም “ጅብሪል መጥቶ ጠራኝ። ለጥሪው ምላሽ ሰጠሁ። እንቅልፍ የወሰደሽ መሰለኝ። ልቀሰቅስሽ አልፈለግኩም። ምክንያቱም ትፈሪያለሽ ብዬ አሰብኩ። አልበቂ ሄጂ ለሙታን ዱዓ እንዳደርግላቸው አዘዘኝ። ሄድኩ” በማለት የወጠብትን ምክንያት አስረዷት።

አዎ ነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) ደግና አስተዋይ ሰው ነበሩ። የሰዎችን ስህተት አያጎሉም። ሙስሊም እንደዘገቡት ለሰዎች እንዲህ ይሉ ነበር። “ሙእሚን ወንድ ሙእሚን ሴትን አይጠላም። ከሷ ላይ አንድ የሚጠላው ነገር ቢኖር ሌላ የሚወድላት ነገር ይኖራል።” አንዲት ሴት አንድ መጥፎ ባህሪ ወይም ተፈጥሮ ስላለባት አንድ ወንድ በፍፁም ሊጠላት አይገባም። ይልቁንም ያላትን ጥሩ ነገሮች ከግምት ውስጥ በማስገባት ስህተቷን ይቅር ማለት አለበት። በሷ ላይ አንድ ስህተት በሚያይበት ጊዜ በፍጥነት መልካም ነገሮቿን ያስታውሳል። በሷ ላይ አስቀያሚ ነገር ሲያገኝ ወቢቷን ያስባል። በሷ ላይ ለሚያያቸው የማይወዳቸው ነገሮች ግዴለሽ ለመሆን መጣር አለበት።

ሀዳሴ...

ወቀሳ ምክር ለማይቀበል ሰው አይደለም። ይልቁንም ተገቢ ባልሆነ መንገድ ለሚያቀርበው ሰው ነው።



ጥቅሉን ፍታ

ሰዎች ተሰባስበው ስህተት ከሰሩ እንደ ህግ ወዲያውኑ መመከር አለባቸው። ሆኖም አንዳንዴ ጥቅሉን መፍታት ሊያስፈልግ ይችላል። እያንዳንዳቸውን በግል ማነጋገርና መምከር። ለምሳሌ ቤትህ ውስጥ ወጣቶች ተሰብስበዋል። የወንድምህ ጓደኞች ናቸው። ሀራም ነገሮች ወደሚፈፅሙበት ቦታ ለመሄድ ሲያቅዱ ሰማህ። ልትመክራቸው ፈለግክ። ግን እንዴት? አንድ ሁለት ቃላት ወርወር አድርገህ ምክርህን ልትለግስ ትችላለህ። ይህ ግን አመርቂ ውጤት ላያመጣልህ ይችላል። ጥቅሉን ብትፈታውና ዘለላ በዘለላ ብታናግራቸውስ? ይህን ማድረግ ትችላለህ?

ሲሊያዩ ከመካከላቸው ምክንያታዊ ነው የምትለውን ሰው ጠርተህ "እከሌ ሆይ ወደዚህ ቦታ ልትሄዱ እንደሆነ ሰምቻለሁ። አንተ ከሌሎቹ የተሻልክ ሰው ነህ። ወደዚህ ቦታ የሚሄድ ሰው የተለያዩ ችግሮች እንደሚያጋጥሙት ታውቃለህ። በሽታ ይዞ ነው የሚመለሰው። ወደ ሌላ ቦታ እንሂድ የሚል ሃሳብ ብታቀርብላቸው ምን ይመስልሃል? ሀይቆች፣ ወንዞች፣ የባህር ዳርቻና ሌሎች ሀራም የሌለባቸው መዝናኛዎችን ወደምታገኙበት ቦታ እንሂድ በላቸው በለው። ይህን በጥሩ ሁኔታ ከሰማ ወደዚያ ቦታ የመሄድ ፍላጎቱ በግማሽ እንደሚቀንስ ምንም ጥርጥር የለውም። ወደ ሁለተኛው ሰው ሄደህም ተመሳሳይ ነገር ንገረው። ከዚያም ለሶስተኛው ሰው...። አንዳቸው ለሌላው መናገርህን ሳያውቁ። በድጋሚ ሲገናኙ አንዱ ለምን ወደ ሌላ አገር አንሄድም የሚል ሃሳብ ያቀርባል። ሃሳቡን የሚደግፍ ሌላ ሰውም ያገኛል። በዚህ መልኩ አንድን መጥፎ ነገር አስቀረህ ማለት ነው።

ሌላ ምሳሌ እንውሰድ። ልጆችህ ተሰባስበው ጨዋነት የጎደለው ቪዲዮ እየተመለከቱ ደረስክ። እያንዳንዳቸውን በግል መምከር ጥሩ ዘዴ ነው። ይህን ካደረግክ ጉጢያት ከመስራት ታቅባቸዋለህ። ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ህይወት የዚህ ዓይነት ምሳሌ እናገኝ ይሆን?

በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እና በቁረይሾች መካከል የተፈጠረው አለመግባባት እየጠነከረ ሲሄድ ቁረይሾች አሳቸውንና የበኑ ሃሽም ቤተሰቦቻቸውን አገለሏቸው። ማንም ሰው ከበኑ ሀሺሞች እንዳይገዛ፣ ለነሱ እንዳይሸጥና ከነሱ ጋር እንዳይጋባ አዋጅ ታወጀ።

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እና ባልደረቦቻቸው በምድረ በዳ ሸለቆ ውስጥ ተገልለው ተቀመጡ። ችግሩ እየከፋ ሲሄድ የዛፍ ቅጠሎችን መብላት ጀመሩ። ከመካከላቸው አንዱ ወደ መፀዳጃ ሲሄድ ቁራጭ የግመል ቆዳ አገኘ። አጠበና ቀቀለው። ቆራርጠ በውሃ እያማገ ለሶስት ቀናት ያህል ተመገበው። ረሃቡ እስከዚህ ድረስ ነበር። በኑ ሀሺሞችና ሙስሊሞች በዚህ መልኩ የመከራ ወራትን እያሳለፉ ነው። አንድ ቀን ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከሳቸው ጋር ሸለቆ ውስጥ ተገድበው ላሉት አጎታቸው አቡ ጣሊብ "ውድ አጎቴ! አላህ የቁረይሾችን የአዋጅ ወረቀት ለማውደም የእንጨት ትል ልኳል። በአላህ ስም የሚለው ቃል ሲቀር እዚያ ላይ የተካተተው ጨቋኝና አግላይ አሉባልታ ሁሉ ጠፍቷል። ነፍሳቱ ባንተ ስም አላህ ሆይ! የሚለው ሲቀር የቁረይሾችን የአዋጅ ወረቀት በልተውታል" አሏቸው። ይህን የሰሙት አቡ ጧሊብ በጣም ተገረሙና "ጌታህ ነው ይህን ነገር ያሳወቀህ?" በማለት ጠየቋቸው።

"አዎ" በማለት መለሱ።

አሳቸውም "ወላሂ አሁኑኑ ሄጄ ለቁረይሾች ይህን ነገር እነግራቸዋለሁ" አሉ። ሄዱና "ቁረይሾች ሆይ! የወንድሜ ልጅ እንዲህ እንዲህ የሚል ነገር ነግሮኛል። እስቲ የአዋጅ ወረቀታችሁን አምጡት። እሱ የተናገረው ነገር እውነት ከሆነ አድማውን አቁማችሁ አዋጁን ትሸራላችሁ። ዋሸቶ ከሆነ ግን የወንድሜን ልጅ ለናንተ አሳልፌ እሰጠዋለሁ። እንደፈለጋችሁ ታደርጉታላችሁ" አሏቸው። እነሱም ጥሩ ነው በዚህ ሃሳብ እንስማማለን አሉና አዋጁን ሲያዩት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተናገሩት ነገር ትክክል ነው። ሆኖም በከፋታቸው ቀጠሉ።

በኑ ሐሺሞችና በኑ ሙጠሊቦች ሊያልቁ እስኪቃረቡ ድረስ ሸለቆው ውስጥ እንደተገለሉ ቆዩ። ይሁንና ከቁረይሽ ካፊሮች መካከል ጥቂት አዛኝ ሰዎች አልታጡም። ከነሱ አንዱ ሂሻም ቢን አምር ነው። ሂሻም በህዝቦቹ ዘንድ የተከበረ ሰው ነበር። በጨለማ በግመሉ ምግብ እየጫነ ወደ ሸለቆው በመውሰድ ለበኑ ሀሺሞችና ለበኑ ሙጠሊቦች ይሰጥ ነበር። ሸለቆው መግቢያ ላይ ሲደርስ የግመሉን ልጓም ፈትቶ ሸለቆው ውስጥ እስኪገባ ድረስ ያባርረዋል። ቀናት እየጨመሩ ሄዱ። ሂሻም በየቀኑ ለነሱ ምግብ ማድረስ እንደማይችል ተገነዘበ። በተለይ ደግሞ ቁጥራቸው ብዙ በመሆኑ። ስለሆነም ጨቋኙን አዋጅ ለማስቀየር መሞከር እንዳለበት ወሰነ። እንዴት ይህን ማድረግ ይቻለዋል? ቁረይሾች በዚህ አዋጅ ላይ በሙሉ ድምጽ ተስማምተዋል። ጥቅሉን የመፍታትን ዘዴ ለመጠቀም ወሰነ። ምን አደረገ?

ወደ ዙህይር ቢን አቢ ኡመያ ሄደ። እናቱ ኢቲካ ቢንት አብደል ሙጠሊብ ናት። "ዙህይር ሆይ! አጎቶችህ የምታውቀው መከራ ደርሶባቸው እያለ አንተ እየበላህ እየጠጣህ ማደርን መረጥከን? ከነሱ ጋር ንግድ አይካሄድም። አይጋቡምም። በአላህ

እምላለሁ። እነዚህ ሰዎች የአቡል ሀኪም ቢን ሂሻም /በአማኞቹ ላይ የከፋ ጥላቻ ያለውና የአዋጁ ቀንደኛ ደጋፊ የሆነው አቡ ጀህል/ አጎቶች ቢሆኑ ኖሮ በዚህ ሁኔታ ላይ ባልተዋቸው ነበር" አለው። ዙህይርም "ወይ አንተ እኔ ብቻዮን ምን ማድረግ እችላለሁ? በአላህ እምላለሁ ከጎኔ የሚሰለፍ አንድ ሰው እንኳ ባገኝ አዋጁን ለማስሻር እቆም ነበር" አለው። ሂሻምም "አንድ ሰው አግኝተሃል" አለው።

"ማን ነው?" ሲል ጠየቀው። "እኔ" በማለት መለሰ። ዙህይርም "ሶስተኛ ሰው ያስፈገናል" አለ። ሂሻምም "እሺ። ነገር ግን ጉዳዩን በሚስጥር ያዘው" አለው። ሙጥኢም ቢን አድይ ዘንድ ሄደ። ሙጥኢም አስተዋይ ሰው ነው። እንዲህም አለው፡- "ሙጥኢም ሆይ! ከአብድመናፍ ጎሳ ውስጥ ሁለት ቤተሰቦች ቢጠፉ ደስ ይልሃል አንተ በተገኘህበት ብቻ ሳይሆን ከቁረይሾች ጋር በተስማማህበት ጉዳይ?" ሙጥኢምም "ብቻዬን ምን አድርግ ትለኛለህ?" አለው። ሂሻምም "ሁለተኛ ሰው አግኝቻለሁ" አለው።

"ማን ነው?" ሲል ጠየቀው ሙጥኢም። "ዙህይር ቢን አቢ ኡመያ" አለው። "አራተኛ ሰው ያስፈልገናል" አለ።

"እሺ። ነገር ግን ጉዳዩን በሚስጥር ያዘው" አለው ሂሻም። ሂሻም አቡል በኽተሪ ቢን ሂሻም ዘንድ ሄደና ለሌሎቹ የነገራቸውን ነገር ነገረው። አቡል በኽተሪ ጓጓና "በዚህ ጉዳይ ላይ የሚረዳህ ሰው አግኝተሃል?" ሲል ጠየቀው። "አዎ" አለ ሂሻም። "ማን ነው?" አለው።

"ዙህይር ቢን አቢ ኡመያ፣ ሙጥኢም ቢን አድይ እና እኔ ሁላችንም ካንተ ጋር ነን" አለው ሂሻም። "አምስተኛ ሰው ያስፈልገናል" አለ አቡል በኽተሪ። ከዚያም ዘምዓህ ቢን አስወድ ዘንድ ሄደ። ስለግንኙነታቸውና በሱ ላይ ስላላቸው ሙበት ነገረው።

"በዚህ ጉዳይ የተሰማማ ሌላ ሰው አለ?" ሲል ጠየቀው።

እሱም "አዎ እነ እከሌ እከሌ...አሉ" አለው። ከዚያም የመካ ከፍተኛ ቦታ በሆነው ሀትም አል ሁጁን ላይ ተገናኝተው በምሽት ስብሰባ ለማድረግ ተስማሙ። ተሰብስበው አዋጁን መፃረርና ማስሻር እንዳለባቸው ተስማሙ። ዙህይር "እኔ ንግግሩን እጀምራለሁ። ከዚያ አንድ በአንድ እየተነሳችሁ ተናገሩ" አላቸው። ካዕባ ፊት ለፊት ሰዎች የሚሰባሰቡበት የገቢያ ቦታ ላይ በጠዋት ተገናኙ። ዙህይር ቢን አቢ ኡመያ ጀለብያውን ለብሶ ካዕባን ሰባት ጊዜ ከዞረ በኋላ ወደ ህዝቡ ጠጋ ብሎ ድምጹን ከፍ በማድረግ "የመካ ህዝቦች ሆይ! እኛ ምግብ እንበላለን? ልብስ እንለብሳለን? በኑ ሀሺሞች ግን እያለቁ ነው። እነሱ መግዛትም ሆነ መሸጥ አይችሉም። ወላሂ ይህ የግፍ አዋጅ ሳይቀደድ አርፌ አልቀመጥም" አለ።

ከባልደረቦቹ ጋር ቁጭ ብሎ የነበረውና ይህን ንግግር ያዳመጠው አቡ ጀህል "ዋሸህ! በአላህ እምላለሁ ኢይቀደድም" ሲል ጮኸ።

ዘማህ ቢን አስወድ ተነሳና ድምጹን ከፍ አድርጎ "ይልቁንም አንተ ነህ የዋሸህ። እኛ ይህ አዋጅ ሲፃፍም ደስተኞች አልነበርንም" አለ። አቡ ጀህል መልስ ሊሰጠው ሲል በድንገት አቡል በኽተሪ ተነሳና "ዘምዓህ እውነትን ተናግሯል። በአዋጁ ደስተኞች አይደለንም፤ አልተስማማንም" አለ። አቡ ጀህል ለአቡል በኽተሪ መልስ ሊሰጥ ሲል መጥኢም ቢን አድይ እንዲህ ሲል አምባረቀ። "ሁላታችሁ እውነትን ተናግራችኋል። ከዚህ ውጪ የተናገረ ዋሸቷል። ከዚህ አዋጅና በሱ ውስጥ ከተካተተው መልእክት ሁሉ በአላህ ፊት ራሳችንን ነፃ አውጥተናል!" አለ። ሂሻም ቢን አምርም ተነሳና ተመሳሳይ ነገር ተናገረ። አቡ ጀህል ግራ ገብቶት ፀጥ ብሎ ከቆየ በኋላ "ይቺ ባንድ ጀንበር የተወሰነችና በሌላ ቦታ የታቀደች ነገር ናት" አለ። አል መጥኢም ቢን አድይ አዋጁን ለመቅደድ ወደ ካዕካ ሄደ። "በአንተ ስም አላህ ሆይ!" የሚለው ሲቀር ሌላው የለም።

ብልህ ሁን...

ልምድ ያለው ዶክተር አካልን በእጆቹ ከነካካ በኋላ ነው መርፌ የሚወጋበትን ተገቢ ቦታ የሚመርጠው።